Government of Western Australia
Department of Health

Amharic

# ጥበቃ በሚደረግባቸው ባሕር ዳርቻዎች፤ በባንዲራዎች መካከል የሚገኘውን ሥፍራ ከሲጋራ ጪስ የፀዳ ለማድረግ

ከ22 ሴፕተምበር 2010 ጀምሮ አዲስ የወጣ የሲጋራ ማጨስ ማእቀብ

## በምእራብ አውስትራሊያ ጥበቃ በሚደረግባቸው የባሕር ዳርቻዎች ሲጋራ እንዳይጨስ ተግባራዊ ሆኗል።

ማንኛወም ግለሰብ ጥበቃ የሚደረግባቸው መሆኑ በተመለከተባቸው በባንዲራዎች መካከል ወይም ሌሎች ምልክቶች ባሉባቸው የባሕር ዳርቻ የመዋኛ ሥፍራዎች ሲጋራ ማጨስ የለበተም።

ጥበቃ የሚደርግባቸው የመዋኛ የባሕር ዳርቻዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚከተሉት ዓይነት ምልክቶች ይደረግባቸዋል።

- ሕይወትአዳኞች (Lifesavers) እና ህይወትጠባቂዎች (lifeguards) ይኖራሉ፤
- ሁለት ቀይና ቢጫ ባንዲራዎች በባሕሩ ዳርቻ ይደረጋሉ፤
- ባንዲራዎቹ የሚያመለክቱት በመካከላቸው ባለው ሥፍራ መዋኘት ችግር እንደማያመጣ ነው።

ማጨስ የሚከለከለው ባንዲራዎቹ እቦታው ላይ ሲኖሩ ብቻ ነው።.

### ምልክቶች

የአካባቢው መዘጋጃ ቤቶች፤ ጥበቃ በሚደረግባቸው የባሕር ዳርቻዎች ሲጋራ ማጨስ ክልክል መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ሊያደርጉ ይችላሉ።

### ተፈጻሚ ነት

- የአካባቢ መንግሥታት በባሕር ዳርቻ ማጨስ ያለመቻሉን በተግባር ላይ እንዲውል የማድረግ ተቀዳሚ ሃላፊነት አለባቸው፤
- የአካባቢ መዘጋጃ ቤቶች፤ አዲሱ ደንብ፤ የከባቢ የጤና መኮንኖችን ወይም ተጨማሪ መኮንኖችን፤ ለምሳሌ ሬንጀርስ በመቅጠር ደንቡ ተፈጻሚ እንዲሆን እንዲረዳ ማድረግ ይችላሉ፤
- በፈቃዳቸው የሚያገለግሉ ሕይወት አዳኞች (lifesavers) ደንቡን የማስፈጸም ግዴታ የለባቸውም።

ይህንን ጉዳይ አጽንኦ መስጠት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ደንቡ ሲደነገግ የህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ ነበረው። ካለፉት ልምዶች እንደምንረዳው፤ አብዛኛዎቹ የምእራብ አውስትራሊያ ኗሪዎች ደንቡን ተፈጻሚ እንደሚያደርጉት ይጠበቃል።

### መቀጮ

በባንዲራዎቹ መካከል የሲጋራ ያለማጨሱን ደንብ በተላለፈ ግለሰብ ላይ የሚከተሉት መቀጮዎች ይጣሉበታል፤

- በፍርድ ቤት የሚጣለው ከፍተኛው መቀጮ $1000
- ደንቡን የመተላለፍ ማስጠንቀቂያ $200

ለተጨማሪ መረጃ የትንባሆ ቁጥጥር ቅርንጫፍ ቢሮን ያነጋግሩ፤

ስልክ ቁጥር: 1300 784 892

ኢሜል: tcb@health.wa.gov.au

**Disclaimer:**

The information contained in this factsheet has been produced as a guide only.
To view the full details in the relevant Tobacco Control legislation,
visit www.health.wa.gov.au/tobaccocontrol